# ዜና አዲስ ፀረ-ሙስና

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥነ ምግባርና ፀረ - ሙስና ኮሚሽን
Addis Ababa city administration Ethics & Anti- corruption commission
2015

ቅጽ 2 ቁጥር 1

ህዳር 2016

## ለሙስናና ብልሹ አሰራር ምንጭ የሆነውን የስነ ምግባር ዝቅጠት ለመቀነስ የሃይማኖት ተቋማት ሚና ከፍተኛ መሆኑ ተገለፀ



የመግባቢያ ስምምነት ሰነዱ በተፈረመበት ወቅት

የአዲስ አበባ ስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ከአዲስ አበባ የሃይማኖት ተቋማት ጉባዔ ጋር ሙስናን ለመከላከልና ትውልዱን በስነ ምግባር ለመገንባት በጋራ ለመስራት የሚያስችል የስምምነት ሰነድ ተፈራረሙ፡፡ በፊርማ ስምምነት ስነ ስርዓቱ ላይ የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ሰላም ፍትህ እና መልካም አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶ ሙሉነህ ደሳለኝ  የስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን በአጭር ጊዜ የተመሰረተ ቢሆንም ሙስናን ለመከላከልና በስነ ምግባር የታነፀ ዜጋ ለመፍጠር በርካታ ተግባራትን እያከናወነ መሆኑን ገልፀው የሙስና ወንጀልን ለመቅረፍ ተጠያቂነት በማስፈን ብቻ ሳይሆን ከባለድርሻ አካላቶች ጋር ተቀናጅቶ በማስተማር ዘላቂ ውጤት ማምጣት ይቻላል ብለዋል፡፡

የአዲስ አበባ ስነምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር አቶ ጀማል ረዲ በበኩላቸው በአሁኑ ገዜ በዓለምም ሆነ በሀገር አቀፍ ደረጃ ሙስና ውስብስብና አስቸጋሪ እየሆነ መምጣቱን ገልፀው ችግሩን ከስር መሰረቱ ለመፍታት የሃይማኖት ተቋማት በስነ ምግባር ቀረፃ ስራ  ላይ መረባረብ ይገባቸዋል ብለዋል፡፡

ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## የትምህርት ተቋማት የትውልድ ስነ ምግባር ግንባታ ሚናቸውን ውጤታማ በሆነ መልኩ መወጣት እንደሚገባቸው ተገለፀ



ከግራ ወደ ቀኝ ም/ኮሚሽነር አሰፋ ቶላ፣ ኮሚሽነር ጀማል ረዲ እና
የት/ቢሮ ም/ቢሮ ኃላፊ ወ/ሮ ታጋይቱ ይፍሩ ውይይቱን ሲመሩ

የአዲስ አበባ ከተማ የስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን በየደረጃው ከሚገኙ የትምህርት አመራሮችና ከግብረ ገብ መምህራን ጋር ውይይት አካሄደ፡፡

"የትምህርት ተቋማት የሞራል እሴቶችን ለማስፈፀም ያላቸው ሚና" በሚል የተዘጋጀውን የውይየይት ሰነድ የኮሚሽኑ የስነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ስልጠና ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ጀንበሩ ኢርኮ አቅርበዋል፡፡

ወደ ገጽ 5 ዞሯል

**ሙስና ስጋት የማይሆንባት አዲስ አበባን እንፈጥራለን!**

# የኪነ ጥበብ ባለሙያዎች የማህበረሰቡን ሥነ-ምግባር በመገንባት ረገድ ያላቸው ሚና ከፍተኛ መሆኑ ተገለፀ



ከኪነጥበብ ባለሙያዎች ጋር የፓናል ውይይት ሲካሄድ

የአዲስ አበባ የሥነ-ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን “የሚታመንና የሚተማመን ትውልድ ለመፍጠር የኪነ-ጥበብ ባለሙያዎች ሚና” በሚል መሪ ቃል የፓናል ውይይት አካሄደ፡፡

የአዲስ አበባ የሥነ ምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽኑ ምክትል ኮሚሽነር አቶ አሰፋ ቶላ በውይይቱ ወቅት እንደገለፁት ኪነ-ጥበብ የሰው ልጆች ባህሪ በመቅረፅ ከፍተኛ ሚና የሚጫወት ሲሆን በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን መልካም ሥነምግባር ለማጎልበትና መጥፎ ባህሪዎችን ለማስወገድ የማይተካ ሚና አለው ብለዋል፡፡

ትውልድን በሥነ-ምግባር መገንባት ሀገርን መገንባት ነው ያሉት ምክትል ኮሚሽነሩ የኪነጥበብ ባለሙያዎች ግብረ-ገባዊ ሥነ ምግባር አርአያነት ከራሳቸው ጀምሮ በማሳየት ተንሰራፍቶ የሚገኘውን ስግብግብንት፣ ግለኝነት፣ ሌብነት፣ ስንፍናና ግዴለሽነት ሊዋጉ ይገባል ብለዋል፤

በፓናል ውይይቱ ላይ የተገኙ የኪነጥበብ ባለሙያዎች በመወከል ንግግር ያደረጉት አርቲስት ጥላሁን ጉግሳ እንደተናገሩት የሥነ-ምግባር ግንባታ የሚጀምረው ከቤተሰብ ነው፡፡ የኪነጥበብ ባለሙያዎችም ቤተሰብ ላይ ትኩረት በማድረግ መሥራት ይገባል ብለዋል፡፡ አያይዘውም የኪነጥበብ ባለሙያዎች ቢዝነስ ላይ ከሚያተኩሩ ማህበረሰብ ግንባታ ላይ ቢያተኩሩ ሀገርን እና ማህበረሰቡን ይጠቅማል ብለዋል፡፡

አርቲስት ፀጋዬ ደንዳና የኦሮሚያ የኪነ ጥበብ ባለሙያዎች ፕሬዝዳንት በበኩላቸው የኪነጥበብ ባለሙያዎች ሁለት ነገር እንዲኖራቸው ይጠበቃል አንደኛ ተሰጥኦ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ መልካም ሥነምግባር ነው፡፡ አያይዘውም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተለይ ከ80ዎቹ ወደዚህ አጠቃላይ ማህበረሰቡ ውስጥ ያለው ሥነምግባር እንዲሸረሸር ተደርጓል፡፡ በመሆኑም መንግስት በሁሉም ማህበረሰቡን ሥነ-ምግባር ከሚገነቡ አካላት ጋር የተቀናጀ ሥራ መሥራት ይገባዋል፡፡ ከጎን ሆነው ለማገዝ ዝግጁ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

የሀገር ፍቅር በአፍ ብቻ አይደለም በተግባር መገለፅ አለበት ያሉት ደግሞ አርቲስት ቀመር የሱፍ ሲሆኑ በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን ሥነምግባር ለመለወጥ ሁሉም ኃላፊነት አለበት ብለዋል፡፡ ኪነጥበብ የሰውን ልጅ ሊያበላሽ፣ ሊያለማና ሊያስተኛ ይችላል ያሉት አርቲስቱ ሁሉም አካላት ተቀናጅቶ የሚሰራ ከሆነ ከኛ የተሻለ ትውልድ መፍጠር እንደሚቻል አመላክተዋል፡፡

## ማውጫ

1. የኪነ ጥበብ ባለሙያዎች የማህበረሰቡን ሥነ-ምግባር... 2
2. የሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ተግባር ውጤታማ እንዲሆን.... 3
3. የስነ ምግባር ግንባታ ስራዎችን በማጠናከር ሙስናን.... 4
4. ኮሚሽኑ የተቋማትን የሙስና ተጋላጭነት ስጋት ቅኝት... 5
5. ኮሚሽኑ የሚታመንና የሚተማመን ትውልድ ለመፍጠር.... 6
6. የስነ ምግባርና ፀረ-ሙስና አስፈፃሚዎች ስራቸውን ... 7

በስነ ምግባር ሚዲያና ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት የተዘጋጀ

አድራሻ
በአራዳ ክ/ከ ወረዳ 1 ቸርችል ጎዳና
ትንሳኤ ህንፃ 4ተኛ ፎቅ
ጥቆማ ለመስጠት
የነፃ ስልክ መስመር
8887
እንዲሁም በመስመር ስልክ
011 126 61 87
011 126 61 72
Addis Ababa Ethics and Anti-Corruption -ፀረ ሙስና
Addis Ababa Ethics Media
aanticoruption@gmail.co

# የሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ተግባር ውጤታማ እንዲሆን በቅንጅት መስራት እንደሚገባ ተገለፀ



የስልጠና ተሳታፊዎች በከፊል

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የስነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሀብት ማሳወቂያና ማስመዝገቢያ አዋጅ ቁጥር 668/2002 መሰረት በማድረግ ለሚከናወነው የሀብት ምዝገባ ቅድመ ዝግጅት ውይይት ተደረገ።

በውይይቱ የአዲስ አበባ ከተማ የሥነምግባርና ፀረሙስና ኮሚሽን ም/ኮሚሽነር አሰግደው ኃ/ጊዮርጊስ እንደገለፁት የሀብት ምዝገባ ስራው የመንግስት ተሿሚ አመራሮች፣ ተመራጮችና የመንግስት ሠራተኞች ትኩረት ተደርጎ የሚሰራ ሲሆን የሀብት ማሳወቅና ማስመዝገብ ሥራ በዕውቀት፣ በጥንቃቄ እና በተቀናጀ መንገድ መምራት እንደሚገባ አሳስበዋል።

ኮሚሽኑ የሀብት ምዝገባ ለማካሄድ ቅድመ ዝግጅቱን እያጠናቀቀ መሆኑን የገለፁት ምክትል ኮሚሽነሩ የሀብት ምዝገባ ማካሄድና ጥቅም ላይ ማዋል ሙስናን አስቀድሞ ለመከላከል፣ የሙስና ወንጀል ተከስቶ ቢገኝ የምርመራ ሂደቱን ለማቀላጠፍ፣ ግልፀኝነት ለመፍጠር እና በህዝብ ዘንድ አመኔታ ለማግኘት ትልቅ ሚና አለው ብለዋል።

በውይይቱ ከማዕከል እስከ ወረዳ ያሉ የስነምግባርና የፀረሙስና አስፈፃሚ አካላት አመራሮች ተሳታፊ ሆነዋል።

## የስነ ምግባር ግንባታ ስራዎችን.....

ከገጽ 4 የዞረ





የሩብ ዓመቱ ሪፖርት በቀረበበት ወቅት

በኮሚሽኑ ግልፅነት የሰፈነበት የሰዉ ሀይል ስምሪትና ምደባ 30% ለማካሄድ ታቅዶ በጥናቱ የሚያስፈልገው የሰው ኃይል 183 ሲሆን በ3ቱም ዘርፍ 52 ባለሙያ በዝውውር በማምጣት 28.4% ምደባ በማካሄድ ዕቅዱን ከ94.66% ማሳካት የቻለ ሲሆን የተመደበውን በጀት 100% ጥቅም ላይ እንዲውል ለማድረግ ታቅዶ በሩብ ዓመቱ ከተጠየቀው የጥሬ ገንዘብ ፍሰት ጥቅም ላይ እንዲውል የተደረገው 46.42% ሲሆን ከተለቀቀው የጥሬ ገንዘብ 80% ጥቅም ላይ መዋሉ በሪፖርቱ ተጠቁሟል።

የከተማ አስተዳደሩ ለኮሚሽኑ እየሰጠ ያለው ድጋፍ አበረታች መሆኑ፤ ከማእከል እሰከ ወረዳ ድረስ የመከታተያ ክፍሎች ምደባ መካሄዱ፤ በውስን የሰው ሀይል የተሻለ ስራ መስራት መቻሉ፤ ባለው ውስን የሰው ሃይል ሊመዘበር የነበረው የህዝብና የመንግስ ሃብት ማዳን መቻሉ፤ ህብረተሰቡ ወደ ኮሚሽኑም ሆነ መከታተያ ክፍሎች በመቅረብ ጥቆማ በመስጠት ሙስናን ለመታገል እያደረገ ያለው ተሳትፎ እያደገ መምጣቱ፤ በርካታ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች መሰጠታቸው፤ የተቋሙን ስራዎች በሚዲያና በማህበራዊ ትስስር ገጾች የማልማትና ተደራሽ የማድረግ ስራ መሰራቱ፤ በመጀመሪያው ሩብ አመት ዕቅድ አፈጻጸም ወቅት የተገኙ ዋና ዋና ውጤቶች መሆናቸው በሪፖርቱ ተጠቅሷል።

# የስነ ምግባር ግንባታ ስራዎችን በማጠናከር ሙስናን የሚጠየፍ ትውልድ መፍጠር እንደሚገባ ተገለፀ።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥነ ምግባርና ፀረሙስና ኮሚሽን የ2016 በጀት አመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የዕቅድ አፈፃፀም ላይ ከኮሚሽኑ አመራርና ሠራተኞች ጋር ውይይት አካሄደ።

ኮሚሽኑ ለ10,100 ሰራተኞችን ማሰልጠኑን፤ 145 ጥቆማዎችን መቀበሉን እና 126,762,211.00 በገንዘብ እንዲሁም በአይነት 170 የሚደርሱ ጠቅላላ ንብረቶችን በአስቸኳይ ሙስና መከላከል ስራ ማዳን መቻሉን መቻሉን በሪፖርቱ ላይ ተመላክቷል።



የስልጠና ተሳታፊዎች በከፊል

የሥነ ምግባርና ፀረሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ጀማል ረዲ እንደገለፁት የኮሚሽናችን ትልቁ ተልዕኮ ለሙስና ቀዳዳ የማይከፍት የአሰራር ሥርዓት መዘርጋትና የማስፈፀም አቅም ግንባታ ማሳደግ ዋና ዋናዎቹ ናቸው ብለዋል። አያይዘውም ኮሚሽኑ በከተማዋ ውስጥ በተለይ በአሰፈፃሚ አካሉ ላይ የሚስተዋለውን የሥነምግባር ብልሽት ለመቅረፍ እና ለሌሎች አርአያ የሆኑ በስነ ምግባር የታነፁ እንዲሆኑ ዕቅድ ነድፎ እየተሰራ መሆኑን አብራርተዋል።



ኮሚሽነሮች ስብሰባውን በመሩበት ወቅት

ምክትል ኮሚሽነር አቶ አሰፋ ቶላ በበኩላቸዉ ተቋሙን ከማዕከል ጀምሮ እስከ ወረዳ በማደራጀት ለፀረ ሙስና ትግሉ ምቹ ሁኔታ መፈጠሩን ተናግረዋል። ም/ኮሚሽነሩ አክለዉም በቀጣይ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን ቅንጅታዊ አሰራር በማሳደግ የፀረሙስና ትግሉ ውጤታማ ማድረግ ይጠበቃል ብለዋል።

በሌላ በኩል ተቋሙ ቅድመ መከላከል ላይ አተኩሮ እየሰራ መሆኑን የገለፁት ም/ኮሚሽነር አሰግደው ኃ/ጊዮርጊስ የቅድመ መከላከል ሥራውን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመምራት እንዲያስችል የተቋማት የሙስና ተጋላጭነት ደረጃ ጥናት በመካሄድ ላይ ይገኛል ብለዋል። አያይዘዉም በከተማ አስተዳደር ያሉ ተሿሚዎች፤ ተመራጮችና መንግስት ሰራተኞች የሀብት ምዝገባ ሥራ ለማከናወን የሚያስችል የቅድመ ዝግጅት ስራ መጠናቀቁንም ገልፀዋል።

ኮሚሽኑ ከተቋቋመ አጭር ጊዜ ቢሆነውም በፍጥነት ተደራጅቶ ውጤታማ ስራ መሰራቱንና በቀጣይ ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባ በውይይቱ የተሳተፉ አመራርና ሰራተኞች ተናግረዋል።

ወደ ገጽ ዞሯል

## ለሙስናና ብልሹ አሰራር ምንጭ ...

ከገጽ 1 የዞረ

የአዲስ አበባ ስነምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር አቶ ጀማል ረዲ በበኩላቸው በአሁኑ ጊዜ በዓለምም ሆነ በሀገር አቀፍ ደረጃ ሙስና ውስብስብና አስቸጋሪ እየሆነ መምጣቱን ገልፀው ችግሩን ከስር መሰረቱ ለመፍታት የሃይማኖት ተቋማት በስነ ምግባር ቀረፃ ስራ ላይ መረባረብ ይገባቸዋል ብለዋል።

የኮሚሽኑ ምክትል ኮሚሽነር አቶ አሰፋ ቶላ የመግባቢያ ሰነዱን ባቀረቡበት ወቅት እንደጠቆሙት ሁሉም ሃይማኖቶች እውነትን ሰላምን እና ከግጭት መራቅን ለተከታዮቻቸው በማስተማር ግብረ ገብነት እንዲስፋፋ የሃይማኖት ተቋማት የበኩላቸውን ሚና ሊወጡ ይገባል ብለዋል። አክለውም የሃይማኖት ተቋማት በሚያከናውኑት ተግባራት ከሙስና የፀዱ ሞዴል እንዲሆኑና ከዚህ ጎን ለጎን የስነ ምግባር ግንባታ ስራውን ሊሰሩ እንደሚገባ ጥሪ አቅርበዋል።

አዲስ አበባ የሃይማኖቶች ተቋማት ጉባዔ ዋና ፀሐፊ መጋቢ ታምራት አበጋዝ እንደገለፁት በሃይማኖት ተቋማት ጉባዔ ውስጥ ሰባት ቤት እምነቶች በጋራ ለመስራት የተደራጁ ሲሆን ተቋማቱ የስነ ምግባርና የሞራል እሴቶችን ከመገንባት አንፃር ትኩረት አድርገን እንሰራለን ብለዋል።

በስምምነቱ የአዲስ አበባ የስነ ምግባር እና ፀረ ሙስና ኮሚሽንን ለማቋቋም ባወጣው አዋጅ ቁጥር 75/2014 ኮሚሽኑ የተሰጠውን ስልጣን እና ተግባር ለመፈፀም እንዲረዳው በይበልጥም የትውልድ ስነ ምግባርን በብቃት ለመገንባት፣ ሙስናን እና ብልሹ አሰራርን በመከላከል ሙስና በሀገር ላይ የሚስከትላቸውን ፈርጀ ብዙ ችግሮች ህብረሰተቡ እንዲያውቅ በማድረግ፤ የፀረ-ሙስና ትግሉ ዋነኛ ተዋናይ እንዲሆን ለማስቻል፤ በከተማችን የህዝብ ንቅናቄ ለመፍጠር እና ህዝቡ የፀረ-ሙስና ትግሉ ባለቤት እንዲሆን ለማስቻል፤ በተለይ የሃይማኖት ተቋማት መሪዎች ተከታዮቻቸዉ የሆኑትን የሕብረ-ተሰብ ክፍሎችን ስለ ስነ ምግባር ማስተማርና እሴቱን የማስረጽ ትልቅ ኃላፊነት ያለባቸውና በሃይማኖታቸው አስተምህሮም ግዴታቸው በመሆኑ ይህን ኃላፊነታቸውን ለመወጣት የሃይማኖት ተቋማት መልካም ስነ ምግባርን ለማስረፅ እና ሙስና መከላከል ላይ በጋራ ለመስራት ተስማምተዋል።

## የትምህርት ተቋማት የትውልድ.......

ከገጽ 1 የዞረ

በውይይቱ ወቅት የአዲስ አበባ ከተማ ስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር አቶ ጀማል ረዲ ሙስና የሀገር ኢኮኖሚ ከማሽመድመድ ባሻገር ከፍተኛ ማህበራዊ ቀውስ የሚያስከትል አደገኛ ወንጀል መሆኑን ጠቅሰው የዚህ አጥፊ ወንጀል ምንጩ የስነ ምግባር ብልሽት በመሆኑ ይህንን በማረቅ በኩል የትምህርት ተቋማት ሚና ከፍተኛ መሆኑን ገልፀዋል።

የኮሚሽኑ ምክትል ኮሚሽነር አቶ አሰፋ ቶላ በበኩላቸው የትምህርት ተቋማት መልካም ትውልድ መፍጠሪያ ማዕከል በመሆናቸው ሀገራቸውን የሚወዱ፣ ኃላፊነት የሚሰማቸው እና ሙስናን የሚፀየፍ ትውልድ ለመፍጠር በትምህርት ተቋማት ውስጥ የሞራል እሴቶችን ማስረፅ ያስፈልጋል ብለዋል። አያይዘውም በሁሉም ትምህርት ቤቶች የፀረ ሙስና ክበባት በአዲስ መልክ በማደራጀት የሞራል እሴት የሆኑትን ታማኝነት፣ ሚዛናዊነት፣ ግልፀኝነት፣ ፍትሃዊነት፣ ቅንነት፣ የሀገር ፍቅር፣ ሰላም የመሳሰሉትን እሴቶች ለማስረፅ መረባረብ ይገባል ብለዋል።

የአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊ ወ/ሮ ታጋይቱ ይፍሩ በበኩላቸው የትውልድ ስነ ምግባር ግንባታ ተግባር ውስብሰብና ከትምህርት ዘርፉ ባለፈ ሌሎች ባለድርሻ አካልን የሚያሳትፍ ከመሆኑም በላይ ጉዳዩ ለአንድ አካል የሚተው አይደለም ብለዋል። የትውልድ ስነ ምግባር ግንባታ ጉዳይ የምንወዳት ሀገር የሚረከብ ቀና፣



የስልጠና ተሳታፊዎች በከፊል

ሀገርን የሚወድ፣ የማይገባውን የማይፈልግ፣ ህግን የሚያከበር እና ወንጀልን የሚፀየፍ ትውልድ መፍጠር ነው ብለዋል።

በመድረኩ ላይ በከተማችን ውስጥ ከ1.2 ሚሊዮን በላይ ተማሪዎች መኖራቸው የተመላከተ ሲሆን የትምህርት ተቋማት እና መምህራን የስነምግባር ግንባታ ላይ ያላቸው የማይተካ ሚና በመገንዘብ ክበባትን በማደራጀት በመልካም ስነ ምግባር የታነፀ፣ ሀገርን የሚወድ እና ሙስናን የሚፀየፍ ትውልድ ለማፍራት የበኩላቸውን እንደሚወጡ ገልፀዋል።

በውይይቱ ላይ ከ750 በላይ የሚሆኑ በየደረጃው የሚገኙ የትምህርት አመራሮች፣ ሱፐርቫይዘሮችና የግብረ ገብ መምህራኖች ተሳታፊ ሆነዋል።

## ኮሚሽኑ የተቋማትን የሙስና ተጋላጭነት ስጋት ቅኝት በጥናት ሊለይ እንደሆነ ገለፀ





የቅኝት ጥናት ማስጀመሪያ ገለፃ ሲሰጥ

የአዲስ ከተማ አስተዳደር የሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን በተቋማት የሙስና ተጋላጭነት ስጋት ቅኝት ላይ ለሚሳተፉ መረጃ ሰብሳቢዎች ጋር ውይይት አካሄደ።

በከተማዋ የሚገኙ የ38 አስፈፃሚ ተቋማትን የሙስና ተጋላጭነት ስጋት የማጥናት ስራ እንደተጀመረ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ም/ኮሚሽነር አቶ አሰግደው ኃ/ጊዮርጊስ ተናግረዋል።

የጥናቱ አስፈላጊነት የየተቋማቱ የሙስና ተጋላጭነት ባህሪ ስለሚለያይ እያንዳንዱ ተቋም የሙስና ተጋላጭነታቸው ምን ይመስላል የሚለውን በጥናት ለመለየት፤ ከመልካም አስተዳደር፤ ከአገልግሎት አሰጣጥና ከብልሹ አሰራር ጋር ተያይዞ በማህበረሰቡ ዘንድ የሚነሱ ችግሮችን ለመለየት እንዲሁም የተቀናጀ የሙስና ትግል ለማድረግ እንደሚረዳ ም/ኮሚሽነሩ ጠቅሰዋል።

ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# ኮሚሽኑ የሚታመንና የሚተማመን ትውልድ ለመፍጠር የስነ ምግባር ግንባታ ላይ በትኩረት እንደሚሰራ ገለፀ



የአዲስ አበባ ሃይማኖት ተቋማት ጉባዔ መሪዎች

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን የሚታመንና የሚተማመን ትውልድ እንፍጠር በሚል መሪ ሀሳብ ከአዲስ አበባ ከተማ የሀይማኖት ተቋማት ጉባኤ መሪዎች ጋር የፓናል ውይይት አካሄደ፡
የሚታመንና የሚተማመን ትውልድ ለመፍጠር የስነ ምግባር ግንባታ ላይ ትኩረት ሰጥተን እንሰራለን ሲሉ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ጀማል ረዲ ተናግረዋል፡፡ የማህበረሰቡ መልካም እሴቶች ከተገነቡና ህብረተሰቡን በቅንጅት ማሰራት ከተቻለ ሙስናን መሸከም የማይችል ትውልድ መፍጠር ይቻላል ሲሉ ኮምሽነር ጀማል ገልፀዋል፡፡
የሀገራችን እድገትና ልማት እንዳይረጋገጥ ሙስና የሚያደርሰውን ተፅዕኖ ለማስቀረት የሀይማኖት ተቋማት መሪዎች የድርሻቸውን ሚና እንዲወጡ ኮሚሽነሩ አሳስበዋል፡፡
የኮሚሽኑ የስነ ምግባርና አቅም ግንባታ ዘርፍ ም/ኮሚሽነር አሰፋ ቶላ የፀረ ሙስና ትግሉ ውጤታማ እንዲሆን ቤተሰብ፣ ትምህርት ቤት፣ የሀይማኖት ተቋማት፣ ሚዲያና ማህበራዊ ተቋማት በቅንጅት በመስራት ሚናቸውን እንዲወጡ ገልጸዋል፡፡ ቤተ እምነቶች የግብረ ገብ ተቋም በመሆናቸው በትውልድ ግንባታ ስራ ላይ ሙስናን ለመከላከል በዋናነት በስነ ምግባር ግንባታ ላይ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ም/ኮሚሽነሩ ተናግረዋል፡፡
የሀይማኖት አባቶች ለተከታዮቻቸው አርአያ በመሆን፤ በአግባቡ በማስተማር፤ እርስ በርስ በመተማመንና ከሌብነት የፀዱ በመሆንና ሙስናን በመከላከል ሚናቸውን ሊወጡ ይገባል ሲሉ ም/ኮሚሽነሩ ጠቁመዋል፡፡
በፓናል ውይይቱ የተሳተፉ የአዲስ አበባ ከተማ የሀይማኖት ተቋማት ጉባኤ መሪዎች ሙስናን መከላከልና በስነ ምግባር የታነፀ ትውልድ መፍጠር በመንግስት ብቻ የሚተው ባለመሆኑ የበኩላቸውን ድርሻ ለማብርከት በቅንጅት እንደሚሰሩ ተናግረዋል፡፡ ሙስና ሀገርን የሚጎዳ፣ ፈጣሪን የሚያስቆጣና ለራስ ብቻ ከማሰብ የሚመነጭ ተግባር ስለሆነ መንግስትና የሚመለከተው ሁሉ በጋራ ሊሰሩ እንደሚገባ የሃይማት ተቋማት ጉባኤ መሪዎች ጠቅሰዋል፡፡

## ኮሚሽኑ የተቋማትን የሙስና.......

ከገጽ 5 የዞረ

የተቋማትን የሙስና ተጋላጭነት ስጋት ጥናት ለመስራት የተዋቀረው ኮሚቴ ተግባሩን በጥራት ማከናወነ እንዳለበት በኮሚሽኑ የሙስና መከላከል ዳይሬክቶሬት የሙስና መከላከል ጥናት ቡድን መሪ አቶ ዩሐንስ አበበ ለመረጃ ሰብሳቢዎች ገለፃ ባቀረቡበት ወቅት ተናግረዋል፡፡
በመጨረሻም የሙስና መከላከል ዳ/ዳይሬክተር አቶ ደምስ ረጋሳ በጥናቱ ተሳታፊዎች ለቀረቡ ሀሳቦችና ጥያቄዎች ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡ ሁሉም የጥናቱ ተሳታፊዎች ለጥናቱ ውጤታማነት በትኩረት መስራት እንዳለባቸው ዳይሬክተሩ አሳስበዋል፡፡ የኮሚሽኑ አንዱ ተግባር የሙስና ተጋላጭነትን በጥናት መለየት መሆኑን ገልጸው በቀጣይ በከተማዋ ውስጥ የሚገኙ ቀሪ የመንግስት ተቋማት፣ የልማት ድርጅቶች፣ ህዝባዊ ተቋማትና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ላይ በማጥናት ብልሹ አሰራርና ሙስና አስቀድሞ ለመከላከል የሚደረገውን ጥረት እንደሚያጠናክሩ ዳይሬክተሩ ተናግረዋል፡፡

# የስነ ምግባርና ፀረ-ሙስና አስፈፃሚዎች ስራቸውን ሲያከናውኑ ህግን መሠረት አድርገው በዕውቀት ሊሰሩ እንደሚገባ ተገለፀ።

ከማዕከል እስከ ወረዳ ለሚገኙ የስነ ምግባርና ፀረ-ሙስና አስፈፃሚዎች በአሰራርና ደንብ፣ በስነ ምግባር መመሪያ፣ በሀብት ምዝገባ፣ በሙስና መከላከል እና በኮሚሽኑ የ2016 በጀት አመት ዕቅድ ለ3 ቀናት ተሰጠ።

የስነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ጀማል ረዲ ለፀረ ሙስና ትግሉ ውጤታማነት ቅድሚያ የኮሚሽኑ የስነ ምግባርና ፀረ ሙስና አስፈፃሚዎች በስነ ምግባር ለሌላው አርአያ መሆን እንዳለባቸው ገልፀዋል። በከተማው ውስጥ ካሉ ሰራተኞችና ተቋማት ጋር በመቀናጀት በስነ ምግባራቸው ምስጉን የሆኑትን እያበረታታን የምንሄድበት አሰራር ይኖራል ሲሉ ኮሚሽነሩ ጠቁመዋል። አስፈፃሚዎች ወደ ስራ ሲገቡ አዋጁን፣ ደንቡን እና መመሪያውን አውቀው ህግን መሰረት በማድረግ ስራቸውን ሊያከናውኑ እንደሚገባ ኮሚሽነር ጀማል ረዲ አሳስበዋል።

አበባ ከተማ ያሉ የመንግስት ሹመኛና ሰራተኞች ሀብት ምዝገባ በትኩረት እንደሚሰራ የገለፁት ም/ኮሚሽነር አስግደው ኃ/ጊዮርጊስ ናቸው።

ሙስናን በመከላከል ረገድ የተሰሩ ስራዎችን በኮሙኒኬሽንና ህዝብ ግንኙነት አግባብ እንዲታገዝ በማድረግ ህዝቡ በሙስና ትግሉ ሚናውን እንዲወጣ ማድረግ አለብን ሲሉ ም/ኮሚሽነሩ አሳስበዋል።

ኮሚሽኑ ተቋሙን በጠንካራ መሠረት ላይ ለመገንባት ሰፋፊ ስራዎችን ሲሰራ የቆየ መሆኑን የገለፁት ም/ኮሚሽነር አስግደው ኃ/ጊዮርጊስ የተቋሙን አሰራር ሥርዓት መዘርጋትና ብቃት ያለው የሰው ኃይል መመደብ ከተሰሩ ስራዎች ዋና ዋናዎች መሆናቸውን ተናግረዋል። ተቋሙን ለስኬት የሚያበቃው ብቃት ያለው የሰው ኃይል ለመፍጠር ደግሞ እንዲህ ያሉ የስልጠና መድረኮች አቅም አሟጦ መጠቀም ያስፈልጋል ብለዋል።



የስልጠና ተሳታፊዎች በከፊል

ሙስና የስነ ምግባር ዝቅጠት በመሆኑ በየደረጃው ያለ ባለሙያ ችግሩን ማስተካከል እንዳለበትና የስነ ምግባር ደንብና መመሪያውን ለሌሎች በማስተማር መመሪያው እንዲከበር ሁሉም ሰራተኛ ሚናውን መወጣት እንዳለበት ም/ኮሚሽነር አሰፋ ቶላ ተናግረው ሙስናን በእውቀት መታገል የሚችል አካል ለመፍጠር እንዲህ ያሉ የስልጠና መድረኮች ሚና ከፍተኛ መሆኑን ገልፀው አስፈፃሚዎች ያገኙትን ስልጠና እንደ ግብዓት በመጠቀም በተቋማቸው ለሚገኙ ባለሙያዎች ስልጠና እንዲሰጡና የሙስና ትግሉን እንዲያሳልጡ ጠቁመዋል።

በ2016 ዓ.ም ከማዕከል እስከ ወረዳ ካሉ የስነ ምግባር ፀረ ሙስና አስፈፃሚዎች ጋር በመቀናጀት ሙስናን በዕውቀትና በመረጃ በመታገል የተሻሉ ተግባራትን እንፈፅማለን ሲሉ ም/ኮሚሽነር አሰፋ ቶላ ገልፀዋል። በበጀት አመቱ በአዲስ

ስልጠናው የአሰራር ደንብ፣ የስነምግባር መመሪያ፣ የሀብት ምዝገባ፣ የሙስና መከላከል እና የኮሚሽኑ የ2016 በጀት ዓመት መነሻ ዕቅድ ላይ ያተኮረ ነው።

### ለቅምሻ

የሚታመን ሚተማመን
ከራሱ አልፎ ለሀገር የሚሆን
ብቁ መሪ ለገባው ቃል የታመነ
ለወጣበት ለሰፊው ህዝብ የወገነ
ምልጃን ጽዩፍ ቅን አገልጋይ
እንዲፈጠር በአዲስ ሰማይ
ምን ቢበዛ መሰናክል
ቢሮክራሲ ጠልፎ የሚጥል
ትልማችን ነው የቆምንለት በዓላማ
ስጋት ሳይሆን ልናጠፋው ከአዲስ አበባ

በአቤል መስፍን

# የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስነ ምግባርና ፀረሙስና ኮሚሽን











አድራሻ በአራዳ ክ/ከ ወረዳ 1 ቸርችል ጎዳና ትንሳኤ ህንፃ 4ተኛ ፎቅ ጥቆማ ለመስጠት የነፃ ስልክ መስመር 8887
እንዲሁም በመስመር ስልክ 011 126 61 87 እና 011 126 61 72

በስነምግባር ሚዲያና ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት የተዘጋጀ